# ኮሎኔል ደመቀ፣ ንግስት ይርጋ፣ ሁሉም የወልቃይት ኮሚቴ አባላት እንደሚፈቱ ፋና ዘገበ

ኮሎኔል ደመቀ፣ ንግስት ይርጋ፣ ሁሉም የወልቃይት ኮሚቴ አባላት እና አሳምነው ጽጌ ስማቸው ተጠቅሶ ከእስር እንደሚፈቱ ፋና ዘገበ

******

በተያያዘ ዜና ሙሉቀን ተስፋው የሚከተለውን ዘግቧል።

በጎንደር ኮ/ል ደመቀ አደባባይ ተሰየመ፤ ጎንደር ቀበሌ 18 በተለምዶ ሸዋ ዳቦ እየተባለ የሚጠራው ቦታ ከዛሬ ጀምሮ ኮሎኔል ደመቀ አደባባይ ተብሎ እንዲጠራ ህዝብ ተስማማ።




ራዴዮ ፋና የሚከተለውን ዘግቧል

የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በወሰነው መሰረት መንግስት በተለያዩ ወንጀሎች ተከሰው የነበሩ ተከሳሾችን ክስ እያቋረጠ መሆኑ ይታወቃል ።

በዚሁ መሰረትም በዛሬው ዕለት የ101 ተከሳሾች ክስ እንዲቋረጥ ተደርጓል።

ከነዚህም ውስጥ 56ቱ የግንቦት ሰባት 41ዱ የኦነግ ተባባሪ ተብለው የተከሰሱ ነበሩ።

አራቱ ደግሞ በኃይማኖት አክራሪነትና ሽብር የተከሰሱ ነበሩ።

ከነዚህም ውስጥ ኮነሬል ደመቀ ዘውዴ ጌታቸው አደመ፣ አታላይ ዘርፉ ንግስት ይርጋና ተሻገር ወልደ ሚካኤል ይገኙበታል፤

በተያያዘ ዜና በተለያየ ወንጀል ተከሰው የተፈረደባቸው 18 ሰዎች በይቅርታ ቦርድ ጉዳያቸው እነዲታይና በርዕሰ ብሔሩ ጸድቆ እንዲፈቱ ተወስኗል።

ከነዚህም ውስጥ ብርጋዴር ጀነራል ተፈራ ማሞና አሳምነው ጽጌ ይገኙበታል።


Cpitian L.C Alemu
Getnet


ጀነራል ተፈራ ማሞ


ጀኔራል አሳምነው ጽጌ


ኮ/ል ደምሰው ዓንተነህ